በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Democratic Republic of Ethiopia
CIVIL SERVICE COMMISSION

ቁጥር/Ref.No. ሲሰኮ 30/መ36/12/15

ቀን/ Date መስከረም 09 2015

**በዝርዝሩ ለተመለከቱት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በሙሉ**

**አዲስ አበባ፣**

ጉዳዩ፣ በመንግሥት ሠራተኞች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ላይ ተጨማሪ ውሳኔዎችን ስለማስተላለፍ

የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀት ለውጥ መሠረት የመንግሥት ሠራተኞች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 859/2014 ከኮሚሽናችን ህዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር ሲ.ሰኮ/ኮቢ./463/14 በተጻፈ ደብዳቤ መተላለፉ ይታወሳል፡፡

በመሆኑም በየመስሪያ ቤቱ እየተካሄደ ያለው የሠራተኞች ድልድል ያለበትን ደረጃ ለይቶ ያጋጠሙ ችግሮችን መፍትሄ ለመስጠት እንዲቻል ኮሚሽኑ በሚያደርገው ድጋፍና ክትትል እንዲሁም ከሚቀርቡ ጥያቄዎች በአፈጻጸም መመሪያው ላይ ወጥ ግንዛቤ ያልተያዘባቸውና ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ድንጋጌዎች እንዳሉ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም በመመሪያው ያልተሸፈኑና ግልፀኝነት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እየቀረበ ውሳኔ የሚሰጥበት ስለመሆኑ በድልድል አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 30 የተደነገገ ሲሆን በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ተጨማሪ ሰርኩላር ማስተላለፍ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

በዚህም መሰረት፡-

7
መሥሪያ ኃይሉ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

ስልክ/Tel: +251 115 54 96 66/67
ፋክስ/Fax: +251 115549707
Email: contactus@ecsc.gov.et
Website:- www.ecsc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia
ማገልገል ክብር ነው! ድህነትን ለማሸነፍ ማገልገል ደግሞ ድርብ ክብር ነው!
Serving to Beat Poverty is Double Honor!

1. ለቡድን መሪ፣ለዴስክ ኃላፊ፣ለሥራ አስፈጻሚ፣ለዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ለመሪ ሥራ አስፈጻሚ እና ለጽ/ቤት ኃላፊ ላሉ የኃላፊነት የሥራ መደቦች ላይ ለሚወዳደሩ ሠራተኞች ለትምህርት ዝግጅት የተሰጠውን ነጥብ በፈተና ማድረግ የሚፈልጉ መስሪያ ቤቶች ለትምህርት የተሰጠውን 25 በመቶ ነጥብ በፈተና ውጤት በማካተት መጠቀም የሚችሉ መሆኑን፣
2. የተቋማዊ የሥራ አፈጻጸምና የሠራተኛው የሥራ አፈጻጸም በማናበብ የሚያስፈጽም ተቋም ካለ በፈተና የሚደረገው ማወዳደር በሥራ አፈጻጸም ውጤት መሠረት ውድድር ማካሄድ ያልተከለከለ መሆኑን፣
3. አንድ ዕጩ ተወዳደሪ በሚወዳደርበት የሥራ መደብ ተፈላጊ ችሎታ መሰረት በየተዋረድ ያለው የትምህርት መስክ እና የሥራ ልምድ ከሥራ መደቡ ጋር በቀጥታ ተመሳሳይ መሆን ያለበት መሆኑን እንዲሁም
4. አንድ ሰራተኛ ለክፍት የሥራ መደብ ለመወዳደር የስራ መደቡ የተቀመጠውን የተፈላጊ ችሎታዎች በቀጥታ ሲያሟላ ብቻ መሆኑ ታውቆ በዚሁ መሰረት መፈጸም እንደሚቻል በማክበር እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

ግልባጭ

- ለክቡር ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለክቡር ምክትል ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለክብርት ምክትል ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለሠው ሀብት ህጎች ጥናትና ኦዲት ዳ/ጀኔራል
- ለሠው ሀብት ህጎች ጥናትና ስርፀት ዳይሬክቶሬት
- ለሠው ሃብት ኦዲት ዳይሬክቶሬት

ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

1. የግብርና ሚኒስቴር
2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
3. የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
4. የማዕድን ሚኒስቴር
5. የቱሪዝም ሚኒስቴር
6. የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር
7. የገንዘብ ሚኒስቴር
8. የፕላንና ልማት ሚኒስቴር
9. የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
10. የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር
11. የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር
12. የውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር
13. የመስኖና ቆላማ አከባቢ ሚኒስቴር
14. የትምህርት ሚኒስቴር
15. የጤና ሚኒስቴር
16. የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
17. የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር
18. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
19. የፍትህ ሚኒስቴር
20. የሰላም ሚኒስቴር